ግብር ከፋዮች የ 2016 E.C (2023 G.C)በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ስታቀርቡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃዎችን ጭምር እንድታቀርቡ እናሳስባለን፡፡

ከዓመታዊ ንግድ ትርፍ ግብር ማሳወቂያ ጋር የሚቀርቡ መረጃዎችን ስለማሳወቅ

ግብር ከፋዮች የ 2016 E.C (2023 G.C)በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ስታቀርቡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃዎችን ጭምር እንድታቀርቡ እናሳስባለን፡፡

የድርጅቱ ስም፡- _____ **መለያ ቁጥር** _____

ሂሣቡ የቀረበው በ IFRS ☐ **GAAp** ☐ **DRAFT** ☐

የሂሣብ መግለጫው አዲት ከሆነ አዲት ያደረገው የሂሣብ ባለሙያ ሙሉ ስም ይገለጽ፡-

ተ.ቁ	*ዝርዝር*	*ቼክ ሪማርክ*
1	የሂሣብና የኦዲት ሪፖርቶችን ለቦርድ/ለኢትዮጵያ ሂሣብ አያያዝና ኦዲት በርድ አቅርበው እንዲመዘገብ ማድረግ	
2	የንግድ ሥራ ሀብት ትክክለኛው ዋጋ ያልተገኘለት እንደሆነ የንግድ ስራ ሀብት ዋጋ የመገመት ስልጣን ከተሰጠው አካል የተዘጋጀ የዋጋ መግለጫ ሰነድ	
3	በታክስ ዘመኑ የተወገደ የንግድ ሥራ ሀብት የሽያጭ ዋጋ፣ በተፈጥሮ አደጋ ለወደመ ወይም በሌላ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት ለውጥ ለተደረገበት ሀብት የተፈፀመ የካሣ ክፍያ ካለ የክፍያ ማስረጃ ማቅረብ	
4	የታክስ እፎይታ ወይም ከታክስ ነፃ መብት ያለው ታክስ ከፋይ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ	
5	ለታክስ ስሌት የተዘጋጀው በተፈቀደላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች ወይም በውጭ ኦዲተሮች የተሰጠውን የምስክር ወረቀት ከሂሣብ አያያዝ ኦዲት ቦርድ እንዲያቀርቡ ማድረግ	
6	የተሟላ ዓመታዊ የሂሣብ መግጫ /Financial Statement/ ኢንካም ስቴትመንት እና ባላንስ ሽት	
7	ተከፋይ የታክስ ሂሳቦችን /payable/በተመለከተ ክልሎች ላይ ከፍለው ከሆነ መረጃ ይቅረብ	
8	የንግድ ሥራ ሀብት የእርጅና ቅናሽ በወጪነት ስታቀርቡ በነባሩና በአዲሱ አዋጅ መሰረት የተሰራውን ለይታችሁ እንድታቀርቡ	
9	የቅድመ ግብር ክፍያ ተቀናሽ ከአመታዊ ሽያጭ በላይ ከሆነ ዝርዝር ምክንያቱን ከማስረጃ ጋር እንዲቀርብ	
10	ለሰራተኛ የህክምና ወጪ ካወጡ በቅጥር ጊዜ የህክምና ወጪ እንደሚሸፈንለት የሚያሳይ ውል መቅረብ አለበት፣	
11	ለቦርድ አባላት የተከፈለ እንዲሁም ቦነስ ክፍያ እንደ ወጪ እንዲያዝ ግብር የተከፈለበት መሆኑን የሚያሳይ መረጃ መቅረብ አለበት	
12	ለእርዳታ የተሰጠ ገንዘብ እንደ ወጪ እንዲያዝ እርዳታው በአገራዊ ጥሪ የተሰጠ ዕርዳታ ለተፈቀደው አካል መዋሉን የሚያሳይ ደብዳቤና ገንዘቡ ገቢ የተደረገ ደረሰኝ ማቅረብ	
13	በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የተገለፀው ጠቅላላ ሽያጭ/ተሰብሳቢ/ ከተጨማሪ እሴት ታክስ የ 12 ወር ሽያጭ ሂሳብ ጋር ልዩነት ካለው ዝርዝር ምክንያቱ በማስረጃ ማቅረብ	
14	የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ዓመታዊ ሪፖርትና የእጅ በጅ ሽያጭ ማጠቃለያ ዝርዝር በኤክሴል ተሰርቶ እንዲቀርብ	